# Äthiopische Trauerselbsthilfe (Iddir) Nürnberg e.V.

## በኑርንበርግና አካባቢው የኢትዮጵያውያን ዕድር

# መተዳደሪያ ደንብ

# መግቢያ

እንደሚታወቀው እጅግ በጣም ብዙ የሆንን ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ምክንያቶች ሀገራችንን ለቀን በመሰደድ በተለያዩ አህጉራት የምንኖር ሲሆን ከመካከላችንም ጥቂት የማይባሉት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ለሀገራቸው አፈር ሳይበቁ ቀርተዋል፡፡ እንደፍላጎታቸውና እንደወገን ምኞትም ይህ የመጨረሻ የእረፍት ጉዞ በሥነ ሥርዓት ሳይካሄድ መቅረቱ ደግሞ አሳዛኝ እየሆነ ያለው ለቅርብ ዘመዶቻቸው ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም ነው:: ብንተባበር እና በጋራ መቆም ብንችል ኖሮ እንኳንስ የወገኖቻችንን አስክሬን ለሐገሩ አፈር ማብቃት ቀርቶ፤ ሌሎችንም ከዚህ የበለጡ ማሕበራዊ ጉዳዮችን በቀላሉ ማከናወን መቻላችን ለሁላችንም ግልጽ ነው።

ይሕንን ጽኑ እምነታችንን ተመርኩዘንና ከወላጆቻችን በወረስነውን ጠቃሚ ልምድ መሰረት ዕድር ብናቋቁም በሞት ከዚህ አለም የሚለይን ሰው በተለመደው የሐገራችን ስርአት መቅበር አለያም አስከሬኑ ለሐገሩ አፈር እንዲበቃ ማድረግ ከመቻላችንም በላይ ፤ የሟችን ዘመዶች በማጽናናትና የተጫናቸውን የሐዘን ሸክም እንዲቀልላቸው ማድረግ መቻላችን በማመን ፤ እኛ በውጪ አገር የምንኖር ኢትዮጵያውያን፤ ከሀገራችንና ከወገናችን ርቀን የምንገኝ ቢሆንም፤ ይሕንን የወላጆቻችንን ጠቃሚ እሴት መሰረት በማድረግ በውጪ አገር በምንገኝ ኢትዮጵያውያን ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ፤ ሟችን እንደምኞቱና እንደወገኖቹ ፍላጎት ለአፈር የማብቃትም ከፍተኛ የሞራል ግዴታ እንዳለብን በመገንዘብ ይህን ዕድር በማቋቋም የሚከተለውን የዕድር መተዳደሪያ ደንብ አውጥተናል።

## ክፍል 1. የዕድሩ ስምና መቀመጫ

አንቀጽ 1 የዕድሩ ስም "በኑርንበርግና አካባቢው የኢትዮጵያውያን ዕድር" በመባል የሚታወቅ ሲሆን ተቀማጭነቱም ኑርንበርግ ከተማ ውስጥ ሆኖ ማኅበራትን ሕጋዊ በሚያደርገው አምትስ ጌሪሽት ኑርምበርግ - ሬጊስትር ጌሪሽት (የኑርምበርግ አንደኛ ደረጃ ፍርድ ቤት - የምዝገባ ፍርድ ቤት) በምዝገባ ቁጥር VR 201611 ተመዝግቧል።

### 1.1 የዕድሩ አርማ

ዕድሩ አርማ ይኖረዋል፡፡ አርማውም ሁለት ለአካለመጠን የደረሱ ሰዎችና ሁለት ልጆች ያሉት ቤተሰብ ሆኖ በጥቁር ጃንጥላ ስር ሆነው የሚያሳይ ምስል ይሆናል።
ይህም የቤተሰቡ አባላት በዕድሩ ጥላ ስር መሰባሰባቸውን የሚያሳይ ይሆናል።
ከዚህ በተጨማሪም በጃንጥላው የላይኛው ክፍል ላይ የዕድሩ ሥም ከላይ
በአማርኛ ከታች ደግሞ በጀርመንኛ ቋንቋ የሚጻፍ ሲሆን መሐሉ ላይ የኢትዮጵያ ባንዲራ በአራት ማዕዘን ቅርጽ ይሰፍራል።
ይህም የሐገራችንን ማንነት የሚያሳይ ነው።

አርማው ከዚህ በታች የተቀመጠውን ምስል ይመስላል።

**ክፍል 2. የዕድሩ ዓላማዎች**

**አንቀጽ 2. ዕድሩ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል**

2.1 በዕድሩ አባላትና በሥሩ በሚያስተዳድራቸው የቤተሰብ አባላት ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ አስክሬናቸውን ለሀገራቸው ወይም ለሚኖሩበት ሐገር የቀብር ሥነ ሥርዓት ማብቃት።

2.2 በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት "የቤተሰብ አባላት" ማለት ባል እና ሚስት እንደዚሁም በሥራቸው የሚተዳደሩ ዕድሜያቸው 25 ዓመት ያልሞላቸው ልጆቻቸው ማለት ነው።

2.3 ዕድሩ የፖለቲካ እና የሃይማኖት ዓላማዎችን አያራማድም።

2.4 ዕድሩ በተለይ በሞት አደጋ ጊዜ ለመረዳዳት የተቋቋመ ነው። ሆኖም ግን እንደ አስፈላጊነቱ በአንቀጽ 6.6 ሐላፊነት ያስፈጽማል ።

2.5 በአንድ የዕድር አባል ወይም አብረውት በሚኖሩ ቤተሰቦቹ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ አስክሬን ወደ ኢትዮጵያ ለመላኪያ ወይም የዕድሩ አባል በሚኖርበት አገር ለቀብር ማስፈጸሚያ በርካታ የገንዘብ መጠን የሚጠይቅ በመሆኑ፤ ችግሩን በተጠናከረ መልኩ ለመቋቋም ይቻል ዘንድ ከሌሎች የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች (Caritas, Diakonie, እና የመሳሰሉ ሌሎች ተቋማት) ጋር የቅርብ የሥራ ግንኙነት ማድረግ።

**ክፍል 3. የዕድሩ የሥልጣን አካላት**

**አንቀጽ 3. ዕድሩ የሚከተሉት የሥልጣን አካላት ይኖሩታል**

3.1 የዕድሩ ጠቅላላ ጉባኤ

3.2 የዕድሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

3.3 የዕድሩ የኦዲተሮች ኮሚቴ

**ክፍል 4. የዕድሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ኃላፊነት፤**

## አንቀጽ 4. የዕድሩ ጠቅላላ ጉባኤ

የዕድሩ ጠቅላላ ጉባዔ የዕድሩ ከፍተኛው የስልጣን አካል ሲሆን ምልአተ ጉባኤ የሚባለው የዕድሩ አባላት በሙሉ ወይም አብዛኛው በአንድ የስብሰባ ቦታ ላይ ተገኝተው የሚያደርጉት ጉባኤ ይሆናል የዕድሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከዚህ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል

4.1 የጠቅላላ ጉባኤው ተግባር

ሀ. በአንቀጽ 3 ከንዑስ አንቀፅ 2 እስከ 3 የተገለጹትን የአመራር አካላት የሚመሩ ሰዎችን ከነ 3 ተጠባባቂዎች ጋር ከዕድሩ አባላት መካከል ይመርጣል፡፡

ለ. ዕድሩ የሚመራበትን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል: ያሻሽላል: ይለውጣል እንደዚሁም ተጨማሪ የውስጥ መመሪያዎችን ያጸድቃል፡፡

ሐ. የዕድሩን የተለያየ ዘርፎች እንዲመሩ ጉባኤው የመረጣቸው ሰዎች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በትክክል መወጣታቸውን ሪፖርት ያዳምጣል ይመረምራል ውሳኔ ይሰጣል፡፡

መ. በአመራር አካላት ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤው የመደባቸውን ሰዎች የሥራ ድክመት አሳይተው ከተገኙ ምክንያቶችን መርምሮ የታዩት ድክመቶች እንዲታረሙ ወይም በአመራር ላይ የተመደቡት ሰዎች ከአመራር ቦታቸው ወርደው በምትካቸው ሌሎችን መርጦ ይሰይማል፡፡

ሠ. የሂሳብ ምርመራ የሚያደርግ 3 አባላት ያሉት የኦዲተር ኮሚቴ ያቋቁማል፤ የዕድሩን የገንዘብ ወጪና ገቢ መርምረው ለጉባኤው እንዲያቀርቡ መመሪያ ይሰጣል ሪፖርታቸውንም ያዳምጣል በሚቀርበው ሪፖርት ላይም ውሳኔ ይሰጣል፡፡

4.2 የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ

ሀ. የዕድሩ ጠቅላላ ጉባኤ የሚደረገው በዓመት አንድ ጊዜ ይሆናል:: ነገር ግን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተጠቀሰው ጊዜ ሳይጠበቅ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል:: እንደዚሁም ከዕድሩ አንድ ሶስተኛው ጉባኤ እንዲጠራ ከጠየቁ ጉባኤው ሊጠራ ይችላል::

ለ. ጉባኤው ከመጠራቱ ቢያንስ ከሁለት ሳምንት አስቀድሞ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የጉባኤውን አጀንዳ በመግለጽ ለአባላቱ ጉባኤ የሚካሄድ መሆኑን ማሳወቅ አለበት፡፡

4.3 የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ

ሀ. ጠቅላላ ጉባኤው ሥራውን የሚያከናውነው ከግማሽ በላይ የዕድሩ አባላት በጉባኤው ላይ ሲገኙ ይሆናል፡፡

ለ. ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ምልዐተ ጉባኤው ካልሞላ ሌላ ተከታይ ስብስባ እንዲጠራ ይደረጋል፤ ሆኖም በቀጣዩም ጥሪ ምልዐተ ጉባኤው ሊሞላ ካልቻለ በዚህ ስብሰባ የተገኙት አባላት እንደ ምልዓተ ጉባኤ ይቆጥራል፡፡

ሐ. ጉባኤው በዕለቱ አጀንዳ ላይ ውሳኔ የሚያስተላልፈው በጉባኤው አባላት የድምጽ ብልጫ ነው፡፡ ነገር ግን ድምጽ እኩል ከመጣ ግን ሊቀመንበሩ የደገፈው ወገን ውሳኔ ይጸናል፡፡

መ. በስብሰባ ሥርዓት ሕግ መሠረት ድምጽ አሰጣጥ በግልጽ እጅ በማውጣት ይሆናል:: የምርጫው አፈጻጸም ጠቅላላ ጉባኤው በመረጣቸው ሶስት አባላት ባለው አስመራጭ ኮሚቴ ሲሆን እነዚህም ከሥራ አመራሩና ከእጩዎች ውጭ መሆን አለባቸው፡፡

4.4 ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ የሆኑ ንውሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡

4.5 ጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንበሩ በሌለ ጊዜ በዋና ጸሐፊው ይመራል፡፡

4.6 ሊቀመንበሩም ሆነ ጸሐፊው በማይኖሩበት አጋጣሚ ሊቀመንበሩ ከስራ አሰፈጻሚ አባላት መሐል አንደኛውን በጽሁፍ ሊወክል ይችላል፡፡

## ክፍል 5 የዕድሩ አመራር ኮሚቴዎች

## አንቀጽ 5 የዕድሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

5.1 የዕድሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰባት አባላት ይኖሩታል

እነሱም:- ሊቀመንበር፣ ዋና ጸሐፊ፣ ገንዘብ ያዥ፣ ሂሳብ ሹም፣ የማኅበራዊ ሥራ ዘርፍ ተጠሪ፣ የሕዝብ ግንኙነት ተጠሪ እና አባል ናቸው።

5.2 ዕድሩ በአንድነት፤ በሊቀመንበሩና በጸሐፊው ይወከላል።

5.3 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ ይመረጣሉ፡፡ የስራ ክፍፍላቸውንም በራሳቸው ስምምነት ያከናውናሉ።

5.4 በዕድሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሥራ አስፈጻሚና የኦዲተሮች የሥራ ዘመን 3 ዓመት ይሆናል። ማንኛውም የዕድሩ አባል መመረጥ የሚችለው ለሁለት ተከታታይ የስራ ዘመን ብቻ ይሆናል። ለሶስተኛ ጊዜ ለመመረጥ ቢያንስ አንድ የስራ ዘመን ሳይመረጥ መቆየት ይኖርበታል፡፡

5.4.1 አዲስ የሥራ አመራር ከተመረጠ በኋላ የቀድሞዎቹ ሊቀመንበርና ጸሐፊው የሽግግር ጊዜውን በተሳካ ሁኔታ ለማኪያሄድ ይቻል ዘንድ በጋራ አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎችን ማኪያሄድ ይጠበቅባቸዋል።

5.5 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ ነገር ግን አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ሳይጠበቅ እያንዳንዱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ስብሰባ እንዲጠራ መጠየቅ ይችላል።

5.6 ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መካከል አንዱ ከተሰናበተ ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት በተጠባባቂ ከተመረጡት መካከል ከፍ ያለ ድምጽ ያለው አንዱ ተመርጦ

በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውስጥ ተካቶ እስከሚቀጥለው ምርጫ ድረስ ያገለግላል ። የሚኖረው ሐላፊነትም በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ይወሰናል።

**ክፍል 6 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተግባር**

**አንቀጽ 6 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተግባር**

6.1 አጠቃላይ ተግባር

ሀ. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው መተዳደሪያ ደንቡ በሚያዘውና በአጠቃላይ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት  የዕድሩን እንቅስቃሴ ይመራል።

ለ. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከተመረጡ አመራሮች መሐል በራሱ የሥራ ድልድል ያደርጋል።

ሐ. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ የመገኘት ግዴታ አለባቸው።

መ. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጨማሪ መመሪያዎችን እያወጣ ሥራውን በተግባር ያከናውናል።

6.2 የሊቀመንበሩ ተግባር

ሀ. ሊቀመንበሩ ጠቅላላ ጉባኤውን እና የሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴውን ስብሰባዎች በሊቀመንበርነት ይመራል።

ለ. ሊቀመንበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን የሥራ እንቅስቃሴ ይቆጣጣራል፡

ሐ. ከሌሎች የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመስራት ይሞከራል፡፡

6. 3 የዋና ጸሐፊ ተግባር

ሀ. የዕድሩ ጠቅላላ ጉባኤ ፡ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ስብሰባዎች ሲካሄዱ ቃለ ጉባኤ ይይዛል።

ለ. የዕድሩን ፋይሎችና የተለያዩ ዶክመንቶች ሥርዓት ባለው ሁኔታ እንዲያዙ ያደርጋል።

ሐ. ሊቀመንበሩ በሌለ ጊዜ እሱን ተክቶ ለሊቀመንበሩ የተሰጡትን ኃላፊነቶች ያከናውናል።

6.4 የገንዘብ ያዥ ተግባር

ሀ. በየወሩ መጨረሻ ከአባላት ወርኃዊ መዋጮ በዕድሩ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ መደረጉን ያረጋግጣል።

ለ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለዕድሩ ገቢ ሊሆን የሚገባውን ገንዘብ በዕድሩ የባንክ ሂሳብ ያስቀምጣል።

ሐ. በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔ መሰረት ገንዘብ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ያደርጋል።

መ. ለወጣው የገንዘብ ወጪ አስፈላጊ መረጃዎችንና ደረሰኞችን ይጠይቃል።

ሰ. ከዕድሩ አባላት በባንክ ውክልና መሰረት የሚከፈለው ወርኃዊ መዋጮ ተቋርጦ ሲገኝ ወዲያውኑ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያስታውቃል።

ረ. ገንዘብ ያዡ ከሒሳብ ሹሙ ጋር በጋራ በመተባበር የዕድሩን በጀት ያዘጋጃል ፣ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያጸድቃል እንዲሁም ያንቀሳቅሳል።

6.5 የሂሳብ ሹም ተግባር

ሀ. ከገንዘብ ያዡ ጋር በመተባበር የዕድሩን የገቢና ወጪ ሂሳብ በትክክል እየመዘገበ በመያዝ በየወሩ መጨረሻ እየሰራ ይዘጋል።

ለ. ለጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የሂሳብ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል።

ሐ. በአንቀጽ 6.4 ንዑስ አንቀጽ ረ ያለውን ያሰፍጽማል።

6.6 የማኅበራዊ ሥራ ዘርፍ ተጠሪ ተግባር

የዕድሩ አባል የጤና እክል ወይም ሌላ ተመሳሳይ ችግር ሲያጋጥመው ታማሚው ወይም ችግር የደረሰበት አባል ፈቃደኛ ሆኖ ከተገኘ ለአባላት በማሳወቅ እንዲጠይቁትና አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያገኝ ያደርጋል።

6.7 የሕዝብ ግንኙነት ተጠሪ ተግባር

ሀ. በአንቀጽ 2 ንዑስ ቁጥር 5 ድንጋጌ መሰረት ከተለያዩ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶችን እያደረገ ለዕድሩ የሚጠቅሙ ልምዶችን ያሰባስባል።

ለ. የዕድሩ ቃል አቀባይ ይሆናል፤ መረጃዎችንም ለአባላት ያስተላልፋል።

ሐ. ዕድሩን ለማስተዋወቅና ለማሳደግ የሚረዱ ጽሁፎችን እያዘጋጀ በየቦታው ይበትናል።

መ. ስለ ቀብር ቤቶች፣ ትራንስፖርት፣ ፖሊስ እና ስለመሳሰሉት ከዕድሩ ስራ አስፍጻሚ ጋር ግንኙነት ስላላቸው ተቋማትና አገልግሎቶች አስፈላጊውን ጥናት ያደረጋል እንዲሁም ከሊቀ መንበሩ ጋር በመተባበር የሞት አደጋ ሲያጋጥም ያስፈጽማል

## ክፍል 7 የዕድሩ ኦዲተር ኮሚቴ

## አንቀጽ 7 የዕድሩ ኦዲተር ኮሚቴ

7.1 የዕድሩ ኦዲተር ኮሚቴ

ሀ. የዕድሩ ኦዲተር ኮሚቴ ሶስት አባላት ይኖሩታል።

ለ. የዕድሩ ኦዲተር ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤው ይመረጣል።

ሐ. የዕድሩ ኦዲተር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ብቻ ይሆናል።

መ. የዕድሩ ኦዲተር ኮሚቴ የስራ ዘመን እንደ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው 3 ዓመት ይሆናል:: ማንኛውም አባል በድጋሚ የመመረጥ መብቱ የተጠበቀ ነው።

7.2 የዕድሩ ኦዲተር ኮሚቴ ተግባር

ሀ. የዕድሩን ገንዘብና ንብረት ይቆጣጠራል

ለ. በዓመት አንድ ጊዜ ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል።

**ክፍል 8 የዕድሩ አባላት መብቶች**

**አንቀጽ 8 የዕድሩ አባል ስለመሆን**

8.1 ዕድሩ በኑርንበርግና አካባቢው ነዋሪ  የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በፖለቲካ አመለካከት ፣ በሐይማኖት፣ በጾታና በማንኛውም ሌላ መሰፈርት ልዩነት ሳያደርግ በአባልነት ይቀበላል ። ከአሁን ቀደም በኑርንበርግ ከተማና አካባቢው በቋሚነት ነዋሪ የነበሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሌላ በማንኛውም የጀርመን ፌዴራል ሪፑብሊክ ግዛት ነዋሪ ቢሆኑም አባል የመሆን መብታቸው የተጠበቀ ነው።

8.2 የዕድሩ አባል ሆኖ ለመመዝገብ የሚፈልግ ሰው በዕድሩ የተዘጋጀውን የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ በመፈረም ማቅረብና የመመዝገቢያ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል።

ሀ. የመመዝገቢያ ክፍያውን አባልነቱ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጸደቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ማጠናቀቅ   ይኖርበታል።

8.2.1 የመመዝገቢያ ክፍያ

ሀ. ዕድሩ ሕጋዊ እውቅና ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ በሚቅጥሉት 12 ወራት ውስጥ ከሆነ 100.00 € መመዝገቢያ ይከፍላል።

ለ. ዕድሩ ሕጋዊ እውቅና ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ ከ 13 እስከ 24 ኛው ወር ድረስ ከሆነ 150,00 € መክፈል ይኖርበታል።

ሐ. ዕድሩ ሕጋዊ እውቅና ካገኘበት ጊዜ ከ25 ኛው ወር ጀምሮ የሚገባ ሰው 200,00 € መክፈል ይኖርበታል።

መ. በዚሁ መሰረት በየአመቱ መመዝገቢያው 50,00 ኤውሮ እየጨመረ ይቀጥላል።

ሠ. የመጨረሻው የአባልነት መመዝገቢያ ጣሪያ **600,00** (ስድስት መቶ) ኤውሮ ነው።

8.2.2 በአንቀፅ 8.2.1 የተደነገገው የሚጸናው ዕድሩ በሚመሰረትበት ጊዜ በኑረንበርግና አካባቢው ነዋሪ ለሆኑ ብቻ ይሆናል።

8.2.3 በጀርመን ሐገር አዲስ ለሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን መመዝገቢያው 100,00 € ይሆናል ።

8.2.3. ሀ. በ 8.2.3 የተጠቀሰው የሚፀናው ጀርመን ሐገር ከመጣ/ከመጣች እስከ ሁለት አመት ድረስ ብቻ ይሆናል።

ለ. በሌላ የጀርመን ግዛት ይኖር ለነበረ ሰው ለአካባቢያችን አዲስ የሚባለው እዚህ አካባቢ ከመጣ እስከ አስራሁለት ወር ድረስ ጊዜ ብቻ ይሆናል።

ሐ. አመልካቹ (አመልካቿ) የትዳር ጓደኛ ካለው (ካላት) ወይም በትዳር ጓደኝነት የሚያስመዘግበው አባል ካለው በአካባቢያችን የቆዩበት ጊዜ የሚለው የሚወሰነው ለረዥም ጊዜ በአካባቢያችን በቆየው አባል መሰረት ይሆናል።

8.2.4 የዕድሩ አባል ልጆች 25 አመት ሲሞላቸው በራሳቸው አባል ለመሆን ማመልከት ይችላሉ:: በዚህ ጊዜ የመመዝገቢያ ክፍያ አይኖርም:: ማመልከቻውን ካስገቡበት ጊዜ ጀምሮም ሙሉ የዕድሩ አባል ይሆናሉ።

1. የእድሩ አባላት ልጆች 25 አመት ሳይሞላቸው ልጅ ከወለዱና ከቤተሰባቸው ጋር አብረው መኖር ከቀጠሉ አዲስ የተወለደው ሕጻን ወዲያውኑ የእድሩ አባል ይሆናል።

2. የእድሩ አባላት ልጆች 25 አመት ሳይሞላቸው ልጅ ከወለዱና ከቤተሰባቸው ወጥተው በራሳቸው መኖር ከጀመሩ ወይም ደግሞ ካገቡና ከወጡ በራሳቸው ተመዝግበው የዕድሩ አባል መሆን ይኖርባቸዋል።

3. የእድሩ አባል ልጆች ልጅ ከወለዱና ልጁን ከአያቶቹ ጋር ትተው በስራ ወይም በሌላ ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ ሄደው መኖር ቢጀምሩ፤ ሐገርም ውስጥ ይሁን ከሐገር ውጪ ቢሆኑ የልጅ ልጃቸው የዕድሩ አባል ይሆናል።

4. ይሕ ሕግ ከመውጣቱ አስቀድሞ 21 አመት ሞልቷቸው ከእድሩ የተሰናበቱና አባልነታቸውን ማስቀጠል ያልፈለጉ የዕድሩ አባላት ልጆች፤ በዚህ በተሻሻለው የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8.2.4 መሰረት ተመልሰው አባል በመሆን መቀጠል ይችላሉ።

   4.ሀ. አንድ ልጅ 21 አመት ሞልቶትና አባልነቱን ማስቀጠል ሳይፈልግ ቀርቶ ከአባልነት ተሰርዞ ከነበረና አሁን ግን በዚህ በተሻሻለው የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8.2.4 መሰረት ተመልሶ አባል በመሆን መቀጠል ከፈለገ 21 አመት ሞልቶት አባልነቱ ከተቋረጠበት ጊዜ አንስቶ ይህ ሕግ እስከሚጽድቅበት ጊዜ ድረስ ያለውን የአባልነት ክፍያ መፈጸም ይኖርበታል።

5. ወላጆች ልጆቻቸው 25 አመት ሳይሞላቸው በራሳቸው መተዳደር ከጀመሩ ወይም ደግሞ ቋሚ ሥራ የሚሰሩ ከሆነ ለዕድሩ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ላይ ያሉ ልጆች እራሳቸው የአባልነት ፎርም በመሙላት የእድሩ አባል መሆን ይኖርባቸዋል።

6. 25 አመት የሞላቸውና በጤና ምክንያት ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚኖሩ የእድሩ አባላት ልጆች የእድሩ አባልነታቸው እንደተጠበቀ ይቆያል።

8.2.5 ባልና ሚስት በሕግ ሲለያዩና በተናጠል በአባልነት መቀጠል ሲፈልጉ የአዲስ አባል መመዝገቢያ ክፍያ ሳይጠየቁ አዲስ ፎርም በመሙላት አባልነታቸውን በተናጠል ይቀጥላሉ።

8.2.5.1. የእድሩ አባላት የሆኑ ቤተሰቦች በተለያየ ምክንያት ቢለያዩ ልጆቻቸው በፍርድ ቤት የአሳዳጊነት መብት ተሰጥቶት እንዲያድጉ በተወሰነለት አባል ስር አባል ሆነው እንዲቀጥሉ ይደረጋል።

8.3 ሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ አንድ አመልካችን የዕድሩ አባል አድርጎ የሚቀበልበትን ውሳኔ የሚሰጠው በአንቀጽ 8.2 በተደነገገው መሰረት የመመዝገቢያ የከፈለበትን ደረሰኝ እና በየወሩ የአባልነት መዋጮ በዕድሩ ባንክ ውክልና (Dauerauftrag) የሰጠበትን ማረጋገጫ ካቀረበ በኋላ ነው።

8.3.1 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ለአመልካቹ ማስረጃውን ባቀረበ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የውሳኔ መልስ መስጠት አለበት

8.3.2 አመልካቹ በ8.3 የተዘረዘሩትን አሟልቶ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ አባል ይሆናል።

8.4 የዕድሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አዲስ ስለተቀበላቸውና ከዕድሩ ስለተሰናበቱ አባላት ጉባኤ በሚኖር ጊዜ ለጠቅላላው ጉባኤ ሪፖርት ያቀርባል።

8.5 አንድ አባል ከዕድሩ አባልነት የሚወጣው በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔ ወይም በራሱ ፈቃድ በጽሁፍ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ከጠየቀ ወይም ደግሞ በአንቀጽ 9 ንዑስ ቁጥር 5 እና 8 ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል።

8.6 ከዕድሩ በማንኛውም መልኩ የሚሰናበት አባል የከፈለው ገንዘብ አይመለስለትም።

8.7 እያንዳንዱ የዕድር አባል በዕድሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ሐሳብን የመግለጽ የመምረጥና የመመረጥ መብት አለው

8.8 በዕድሩ አባል ላይ ወይም ቤተሰቦቹ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ የቀብር ስነ ስርዓቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጸም ከሆነ ዕድሩ አስከሬኑን እስከ አዲስ አበባ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ሙሉ ወጪ ይከፍላል።

8.8.ሀ ዕድሩ አስከሬኑ አዲስ አበባ ከደረሰ በኋላ ለሚኖረው ውጪ 500.00 € ተጨማሪ እርዳታ ይሰጣል።

8.8.ለ የቀብር ስነስርአቱ በአንቀጽ 8.8 ከተጠቀሰው ውጪ በማንኛው ሌላ አካባቢ የሚፈፀም ከሆነ ዕድሩ በአንቀጽ 8.8 እና 8.8.ሀ የተጠቀሱትን ሃላፊነቶች ይወጣል።

8.8.ሐ የቀብር ስነስርአቱ በአንቀፅ 8.8.ለ በተጠቀሰው መሰረት የሚፈፀም ከሆነና በአንቀፅ 8.8 እና 8.8.ሀ ከተጠቀሰው ወጪ ጋር ልዩነት የሚኖር ከሆነ፤ የሚጨመር ካለ አባሉ እራሱ የመሸፈን ግዴታ አለበት፤ ወይም ደሞ በዚሁ መሰረት የሚተርፍ ገንዘብ ካለ ዕድሩ ለአባሉ በጥሬ ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት።

8.8.መ. አንድ አባል በሕይወት አለመኖሩ የሚገመትበት ሁኔታ ቢፈጠርና ሆኖም ግን አስከሬኑን ማግኘት ካልተቻለ ከሚመለከተው መንግስታዊ አካል በሕይወት አለመኖሩን የሚመሰክር ሕጋዊ የሆነ ማረጋገጫ ሲቀርብለት፤ ዕድሩ በ 8.8 እና በ 8.8. ሀ የተጠቀሱትን ሀላፊነቶች የመወጣት ግዴታ ይኖርበታል።

8.8.ሠ. የአስከሬን ሽኝቱን ሌላ ሶስተኛ ወገን በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ የሚሸፍን ከሆነ ዕደሩ በ8.8 እና በ8.8ሀ የተጠቀሰውን ለአባሉ በጥሬው ይከፍላል።

## ክፍል 9 የዕድሩ አባላት ግዴታዎች

### አንቀጽ 9 የዕድሩ አባላት ግዴታዎች

9.1 የዕድሩ አባል ዕድሩ በሚያዘጋጀው የአባልነት ቅጽ ላይ የቤተሰቡን አባላት ዝርዝርና የአደጋ ጊዜ ተጠሪውን ስምና ስልክ ቁጥር ሞልቶ ማቅረብ አለበት፡ ፡ በሌላም መልኩ የዕድሩ አባል በቤተሰቡ ላይ የሚኖረውን ለውጥ በአንድ ወር ውስጥ ለዕድሩ ማሳወቅ አለበት።

9.2 እያንዳንዱ አባል የዕድሩን ወርኃዊ መዋጮ በወቅቱ የመክፈል ግዴታ አለበት።

9.3 የዕድሩ አባል መረዳዳት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሲጠይቅ የመተባበር ግዴታ አለበት።

9.4 የዕድሩን ጠቅላላ ጉባኤ መካፈል አለበት።

9.5 የዕድሩ አባል በባንክ በኩል የሚያደርገውን ወርኃዊ መዋጮ ለ 3 ወራት በተከታታይ ካቋረጠ የሥራ አስፈጻሚ ከሶስተኛው ወር መጨረሻ ጀምሮ ወርኃዊ መዋጮ ማቋረጡን መሰረት በማድረግ ከዕድሩ የተሰናበተ ስለመሆኑ ውሳኔ ይሰጣል:: ነገር ግን ይህንን ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት ለአባሉ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይጽፋል ወይም ጠርቶ ያነጋግራል።

9.6 በአንቀጽ 9.5 መሰረት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በዕድሩ አባልነት ለመቀጠል ፍላጎት ያለው መሆኑን አባሉ በጽሁፍ ከጠየቀ 30,00 € መቀጫ እንዲሁም ያለበትን ወርኃዊ መዋጮ ውዝፍና ወርኃዊ የአባልነት መዋጮውን ለመክፈል ለባንክ ቋሚ ውክልና (Dauerauftrag) የሰጠበትን ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

9.7 የዕድሩ አባል በአንቀጽ 9.5 መሰረት የወርኃዊ መዋጮ ሊከፍል ያልቻለበትን በቂ ምክንያት ማስረጃ ወይም ማረጋገጫ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ካቀረበና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ካመነበት በአንቀጽ 9.6 መሰረት የሚጣለው የ 30,00 € መቀጫ ተፈጻሚ አይሆንም።

9.8 አንድ የዕድር አባል ዕድሩን የሚጎዳ ድርጊቶች ሲፈጽምና ከዕድሩ አባላት ወይም ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጥቆማ ወይም ማስረጃ ሲቀርብ ጉዳዩን መርምሮ ከዕድሩ እንዲሰናበት ውሳኔ የሚሰጠው የዕድሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲሆን ውሳኔውን ለጠቅላላው ጉባኤው ያሳውቃል።

9.8.ሀ አባሉ ውሳኔውን በመቃውም ውሳኔው በደረሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተቃውሞውን ማቅረብ ይችላል።

9.8.ለ ተቃውሞው መቅረብ ያለበት በጽሁፍ መሆን አለበት።

9.8.ሐ አባሉ ከዕድሩ የተባረረው በዲስፕሊን ጉድለት ከሆነ ተቃውሞው በቀረበ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና የቁጥጥር ኮሚቴው በጋራ አይተው ውሳኔ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

9.8.መ አባሉ በአንቀጽ 9.8.ሐ በተጠቀሰው መሰረት በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና በቁጥጥር ኮሚቴው የጋራ ውሳኔ የማይስማማ ከሆነ ውሳኔው በደረሰው በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ አሁንም በፅሁፍ ለአጠቃላይ ጉባኤው ተቃውሞውን ማቅረብ ይችላል።

9.8.ሠ አባሉ ተቃውሞ በሚያቀርብባቸው ጊዜያት ሁሉ የሚቀጥለው አካል ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ቀድሞ የወሰነው አካል ውሳኔ የፀና ይሆናል።

## ክፍል 10 ስለ ወርኃዊ የአባልነት ክፍያ

### አንቀጽ 10 የአባልነት ክፍያ

10.1 የዕድሩ የአባልነት ወርኃዊ ክፍያ 5,00 € ነው።

10.2 የዕድሩ አባል ሆኖ የተመዘገበ ሰው ለዕድሩ የተመደበውን የአባልነት ወርኃዊ ክፍያ በዕድሩ ባንክ ቋሚ ውክልና (Dauerauftrag) መስጠት አለበት።

10.2.1 የባንክ አካውንት መክፈት የማይችል ወይም የሌለው አባል በጥሬ (ካሽ) ለገንዘብ ያዥ በደረሰኝ መክፈል ይችላል።

10.3 የዕድሩን የአባልነት መዋጮ በዓመት አንድ ጊዜ መከፈል ይችላል:: ይህ ማለትም ዕድሩ የሰጠውን መብት ተጠቃሚ ለመሆንና ከውዝፍ ክፍያ ነጻ ለመሆን ክፍያውን በአውሮፓውያን አቆጣጠር መሰረት ዓመቱ ከጀመረ እስከ ሶስተኛው ወር ማለቂያ ክፍያውን ማጠናቀቅ አለበት።

10.4 የዕድሩን የአባልነት መዋጮ መጠን የሚወስነው የዕድሩ ጠቅላላ ጉባኤ ነው።

## ክፍል 11 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 11 ለዕድሩ አባላት የእርዳታ አሰጣጥ ሥርዓት**

11.1 ዕድሩ በሞት አደጋ ጊዜ በአባሉ ወይም ከእርሱ ጋር አብረውት በሚኖሩ ቤተሰቦቹ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ ሙሉ አገልግሎቱን የሚሰጥው አባሉ ከተመዘገበ ከስድስት ወራት በኋላ ሲሆን ወረሐዊ ክፍያውንም ያጠናቀቀ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

11.2 በዕድሩ አባል ወይም አብረውት በሚኖሩ ቤተሰቦቹ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ የደረሰው አደጋ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው መገለጽ አለበት።

11.3 ዕድሩ የአስክሬን ማጓጓዢውን ሙሉውን መክፈል ያልቻለ እንደሆነና ሌላ እርዳታም ካጣ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ወስኖ ከአባላቱ የድንገተኛ አስተዋጽኦ ጥሪ ማድረግ ሥልጣን አለው።

11.4 የዕድሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በአስክሬን ሽኝት ወቅት በዕድሩ አባል ፍላጎት መሰረት የአሸኛኘት ፕሮግራም ያዘጋጃል።

11.5 ከዕድሩ በራሳቸው ፈቃድ ወይም በዕድሩ ውሳኔ መሰረት የወጡ አባላት እንደገና የዕድር አባልነት ጥያቄ ካቀረቡ እንደማንኛውም አባል በወቅቱ ሊከፍሉ የሚገባቸውን መመዝገቢያ ከፍለው መግባት ይችላሉ።

11.5 ሀ. በአንቀጽ 9.8 መሰረት በዲስፕሊን ጉድለት የወጡ አባላት እንደገና የአባልነት ጥያቄ ካቀረቡ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ይሰጣል።

**አንቀጽ 12 ስለዕድሩ ገንዘብ አጠባበቅ**

**12.1 ዕድሩ በስሙ የተከፈተ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ይኖረዋል**

12.2 የዕድሩ ወርኃዊ ክፍያ በየወሩ መጨረሻ ከአባላት ገቢ መሆኑን ከባንክ ከሚገኘው መረጃ መሰረት የዕድሩ ገንዘብ ያዥ ያረጋግጣል።

12.3 በአባላቱ ፣ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትና በኦዲት ኮሚቴ አባላት ለዕድሩ የሚሰጡ ማናቸውም አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ከክፍያ ነጻ ናቸው።

12.4 በዕድሩ አባል ወይም በሥሩ በሚያስተዳድራቸው ቤተሰቦቹ ላይ የሞት አደጋ በሚደርስበት አጋጣሚና ሌሎችም ማናቸውም ጊዜያት የዕድሩ ወጪ የሚፈፀመው በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት በዕድሩ ሊቀ መንበር እና ገንዘብ ያዥ ፊርማ ይሆናል ። ገንዘቡ በትክክል ስለመውጣቱ የሂሳብ ሹሙ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

12.4.1 ገንዘብ ያዡ ወይም የሂሳብ ሹሙ ሊገኙ በማይችሉበት አስቸኳይ ጊዜ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከኮሚቴው አባላት አንዱን በጽሁፍ ሊወክል ይችላል።

**አንቀጽ 13 የዕድሩ የገቢ ምንጭ**

ከአባላት የሚሰበሰብ ወርኃዊ ክፍያና መመዝገቢያ እንደዚሁም ከበጎ አድራጎት በሚገኝ ዕርዳታ ይሆናል።

**አንቀጽ 14 ስለ ዕድሩ መፍረስ**

14.1. ዕድሩ ሊፈርስ የሚችለው የአባላቱ ቁጥር ከሰባት በታች ከሆነ ብቻ ነው ።

14.2. ዕድሩ ከፈረሰ የዕድሩ አባላት የከፈሉት ክፍያ እንዲመለስላቸው መጠየቅ አይችሉም።

14.3. ዕድሩ ሲፈርስ የዕድሩ ንብረት በጀርመን ሕግ መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኝ በጎ አድራጎት ድርጅት ይሰጣል።

14.4. ዕድሩ በአንቀጽ 14.1 መሰረት ከፈረሰ ይህንን ለማስፈጸም 3 አባላት ያሉት አንድ ኮሚቴ ይቋቋማል።

**አንቀጽ 15 የመተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል**

15.1 የዕድሩን የመተዳደሪያ ደንብ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል የሚቻለው ከጉባኤው አባላት በ2/3 ኛ ድምጽ ሲደገፍ ነው።

15.1.ሀ በአንቀፅ 15.1 የተጠቀሰው ፣ በአንቀፅ 14.1 እና 14.2 የተደነገገውን ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል ተግባራዊ ሊሆን አይችልም።

15.2 በ አንቀጽ 15.1. የተጠቀሰውን ተግባራዊ ለማድረግ በአንቀጽ 4.3.ለ የተጠቀሰው የጸና ይሆናል።

**አንቀጽ 16 የዕድሩ ግዴታ**

16.1 ዕድሩ የጀርመን ፌዴራላዊ ሕጎችንና መመሪያዎችን ያከብራል፡፡

16.2 የአባላቱን ዳታ ( ስም ፣ የመኖሪያ አድራሻ ፣ የኢሜይል አድራሻና ሌሎችም ከአባላት ጋር የተያያዙ የግል ጉዳዮች) በጀርመን የባየር ግዛት ነጻ አስተዳደር ህግ በሚያዘው መሰረት በሚስጢር ይይዛል።

**አንቀጽ 17 ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በዓባላት ጠቅላላ ጉባኤ በ **02.04.2023** ተሻሽሎ ለማኅበራት መዝጋቢ ፍርድቤት - አምትስ ጌሪሽት ኑርምበርግ - ሬጊስትር ጌሪሽት ቀርቦ በመዝገብ ቁጥር **VR201611 በ 21.03.2024** ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ ውሏል።

**ማስታወሻ**፡ በደንቡ ውስጥ በተባዕት የተጠቀሰው ሁሉ ለእንስትም የሚያገለግል ይሆናል።